የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ

TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)

e-mail: ezanareg@hotmail.com

# ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ዴሞክራሲን ዋጠ ?

ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ኢትዮጵያ ውስጥ ብሔራዊ ምርጫ ተካሂዷል ተብለናል ። ይሁን እንጂ "ዴሞክራሲያዊ" እየተባለ የተዘፈነለት ምርጫ ዴሞክራሲውን ውጦ ያጠፋው ይመስል ቆጠራና ውጤት ተበላሸ ተብሎ እየተነገረን ነው።

ይሁን እንጂ ት.ዴ.ት ምርጫው ችግር የገጠመው በቆጠራ ወቅት ነው የሚለውን አባባል ጭራሽ አይጋራም ። ከዴሞክራሲያዊ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ውጤት ሲወለድ እንጂ ራሱን አጠፋ ሲባል አልሰማንም ። የግንቦቱ ምርጫ መጀመሪያውኑ ዴሞክራሲያዊ ሂደትን ተከትሎ የተካሀደ ባለመሆኑ እንጂ በቆጠራ ወቅት ችግር ስለተፈጠረ ተበላሸ ብሎም አያምንም ። እንዲያማ ቢሆን ችግሩን በቀላሉ በዳግም ቆጠራ ማስወገድ ይቻል ነበር ። ችግሩ በቆጠራና በማጣራቱ ሂደት ላይ በተፈጠሩ አለመግባባቶች የተከሰተ አይደለም ። የችግሩ መነሻ የአምባገነኖቹ የኢህአዴግ መሪዎች መስሪ ቀመር ነው ። የችግሩ መነሻ እነሱና ሰፊው ህዝብ ለምርጫ የሰጡት የትርጉም ልዩነት ነው ። እነሱ ስለምርጫ ሲያስቡ የኢትዮጵያን ሰፊ ህዝብ ፍላጎት የሚያንጸባርቅ ነፃና ፍትሓዊ የምርጫ ሂደት ሳይሆን ከምዕራባዊያን የእርዳታ ወይም የብድር ትሩፋት ለማግኘት የሚረዳ የማስመሰያ ምርጫ ነው ። የኢትዮጵያ ህዝቦች ምርጫ ሲሉ ደግሞ በድምጻቸው የሚያስተዳድሩዋቸውን ይበጁናል የሚሉዋቸውን ድርጅቶችን ወይም ግለሰቦችን በነፃ ፍላጎታቸው ለመምረጥ መቻላቸው ነው ። ችግሩ የተፈጠረው አምባገነኖቹ የኢህአዴግ መሪዎች የራሳቸውን የሥልጣን ፍላጎት ከህዝብ ፍላጎት በላይ በማስቀመጣቸው ነው ። እነዚህ አምባገነን መሪዎችና የኢትዮጵያ ህዝቦች ከመጀመርያውም በምርጫው ግብ ላይ ከነበራቸው ልዩነት የሚመነጭ ችግር እንጂ በቆጠራና በማጣራት ሂደቱ ወቅት የተፈጠረ ችግር አይደለም ።

አምባገነኖቹ ምርጫውን ከዚህ በፊት እንደለመዱት በጉልበትና በማጭበርበር ለሥልጣን ማራዘምያ ግባቸው ሊያውሉት ሲፈልጉ ፤ የኢትዮጵያ ህዝቦች ደግሞ በቅታቹሁናል ፤ አየናቹህ ፤ ሞከርናቹህ፤ ካገር ክህደትና ከማጭበርበር ያለፈ ነገር ስታከናውኑ አላየንም ሊሉዋቸው እንደተዘጋጁ ልብ አላሉም። ዳር ድንበርን እንድታስከብሩ ስንጠብቃቹህ ዳር ድንበርን ማስደፈር ፤ ላገርና ለህዝብ ታማኝ እንድትሆኑ ስንጠብቅ አገርና ህዝብን በመናቅ በክህደት መንገድ መጓዝ ፤ ፍትሕና ሥርዓት እንድታሰፍኑ ስንጠብቅ አምባገነንነትን ማስፈን ፤ ባጠቃላይ ካገርና ወገን የሚጠበቅባቹህን ግዳጅ ለመወጣት ባለመቻል በማን አለብኝነትና በዳተኝነት መንገድ ለመጓዝ መርጣቹሀልና በቃቹህኝ ሊላቸው መቁረጡን አልተገነዘቡትም ። አምባገነኖች ሁሌም ቅድሚያ ሰጥተው የሚያዩት የሥልጣን ወንበራቸው እንዳይነካ ማስጠበቅ በመሆኑ የህዝብን ጥያቄ ለማስተናገድና ለመፈጸም አይፈልጉም ። በመሆኑም የኢህአዴግ አምባገነን መሪዎች የህዝብን የሥልጣን ባለቤትነት ሊያረጋግጥ የሚችል ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲያካሂዱ የሚያስችላቸው ገጸ ባሕሪ ሊላበሱ አይችሉም ፤ አልተላበሱምም። ለአምባገነኖቹ ምርጫ ሲባል የህዝብን የሥልጣን በላይነት ለማረጋገጥ የሚደረግ ህዝቡ ከተለያዩ ፕላት ፎርሞች ውስጥ ነፃና ፍትሓዊ በሆነ መንገድ የፈለገውን ለመምረጥ የሚችልበት ነፃ መድርክ መፍጠር ማለት አይደለም ። ለነሱ ምርጫ ሲባል ምርጫ ተካሂዷል ተብሎ በዓለም የመገናኛ ብዙኃን ከተነገረና የዓለም ማህበረሰብም ያንን ተቀብሎ እውቅና ከሰጣቸው ለኢትዮጵያ ህዝቦች ፍላጎትና ምኞት ደንታ የላቸውም ። የኢትዮጵያ ህዝቦች ባለፈው የምርጫ ውጤት ላይ የተሰማቸውን ቅሬታ ወደ ጎን በመተው የኤውሮጳ የምርጫ ታዛቢዎች በሰጡት ምርጫውን የመታዘብ ዘግባ ላይ የስድብ ውርጅብኝ ማንጎድጎዳቸው ይህንን ሃቅ በማያወላውል መንገድ አሳይቶናል ። የኢህአዴግ አመራር እውነተኛ ለአገርና ለወገን የሚቆረቄር ቢሆን ኖሮ ቅድሚያ ማዳመጥ የነበረበት የኢትዮጵያ ህዝቦች እሮሮን ነበር ። ድምፃችን ተሰርቋል የሚሉ ዜጎችን በጥይት በመለብለብ ፋንታ ሰከን ብሎ ቅሬታቸውን ማዳመጥና መፍትሔ መሻት በተገባው ነበር ። ታዛቢዎችን መክሰስና መወንጀል አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝ እንኳ በሁለተኛ ደረጃ ሊመጣ የሚችል ጉዳይ በሆነ ነበር ። ምክንያቱም የምርጫው ውጤት የኢትዮጵያን ህዝብ ፍላጎት

የሚያንፀባርቅ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ የውጭ ታዛቢዎች ዘገባ በምርጫው ሕጋዊነትና ፍትሓዊነት ላይ ሊያሳድረው የሚችል ጫና እጅጉን ውሱን በመሆኑ ነው ። የብዙኃኑ ድምፅ በታፈነበት ሁኔታ ውስጥ የታዛቢዎች ዘገባ ላይ ማልቀሱ የጎላ ትርጉም አይኖረውም ። የውጭ ታዛቢዎች በአዎንታ ያቅርቡት በአሉታ የኢትዮጵያ ህዝቦች ምርጫ ላይ የሚኖራቸው ጫና እጅግ ውሱን ነው ። በዚህ ምክንያትም ዋናው ትኩረት መደረግ የነበረበት የኢትዮጵያ ህዝቦች ውሳኔ ላይ ነው ። ባለመታደላችን ግን እስከ ዛሬ ድረስ እኛን ለማዳመጥ የሚችሉ መሪዎች ማፍራት አልቻልንም ።

በዚህ ምክንያትም የግንቦት 7ቱ ምርጫ ከውጥኑም ቢሆን ነፃ የኢትዮጵያ ህዝቦችን ፍላጎት ለማንጸባረቅ የታቀደ አልነበረም ። ይህ ቢሆን ኖሮ ከመጀመሪያው ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችሉ ገለልተኛ መዋቀሮች መዘርጋት ነበረባቸው ። ነፃ የፍትሕ አካላት መፈጠር ነበረባቸው። ይህ ሳይሆን የቀረው ባጋጣሚ ምክንያት አይደለም። ኢዴኃጎ አሁን የገባንበት ውጥረት ውስጥ እንደምንገባ አስቀድሞ በመገንዘብ እነዚህ መዋቅራዊ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ ከኢህአዴግ ጋር ቢደራደርም ኢህአዴግ የቀረበውን ሓሳብ ለመቀበል ዝግጁ ያልሆነው ችግሩ ሳይገባው ስለቀረ አልነበረም ። ያልተቀበለበት ዋናው ምክንያት የህዝብን ድምፅ ለማፈን የሚያስችለው የበላይነቱን ላለማስነጠቅ ብቻ ነው ። ባይሆን ኖሮ ይህንን ቁልፍ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄ ለመቀበል የማይፈልግበት ሁኔታ ሊኖር ባልቻለ ነበር ። አምባገነኖች በተፈጥሮአቸው የህዝብ የበላይነትን በጣም ስለሚፈሩና በህዝብ ነፃ ምርጫም ስለማያምኑ ከማስመሰል ያለፈ ፋይዳ ያለው ምርጫ ለማካሄድ አይችሉም ። በዚህ ምክንያትም በግንቦት 7 የተካሄደው ምርጫ ግቡን የሳተው በቆጠራና በማጣራቱ ሂደት ወቅት ሳይሆን ከመጀመሪያውም ምርጫን ነፃና ፍትሓዊ ለማድረግ የሚችሉ ቁልፍ ጥያቄዎች ስላልተመለሱ ነው ብሎ ት.ዴ.ት ያምናል ።

ይህንን በዚህ ቋጭተን ወደ ወቅቱ ጥያቄ ስንመለስ የኢህአዴግ መሪዎች አምባገነንነት ከምን ጊዜም በላይ ጎልቶ የወጣበት ሁኔታን እናያለን ። የግንቦት 7 1997 ዓ.ም ምርጫ መሟላት የነበረባቸውን የምርጫ ቅድመ ሁኔታዎች ባይሟሉም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የህዝቡን የለውጥ ፍላጎት በጥልቀት በመገንዘብ የሚካሄደው ምርጫ ውስጥ ለመሳተፍ ወስነው ተሳትፈዋል ። ህዝቡም በነቅስ በመውጣት ቀኑን ሙሉ በመሰለፍ ድምጹን ሰጥተዋል። በዚህ ዓለም ዓቀፍ መስፈርቶችን ባላሟላ ምርጫ ውስጥም ቢሆን ህዝቡ ድምጹን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች በመስጠት የሥልጣን ውክልና ቢሰጣቸውም እንደተጠበቀው አምባገነኑ የኢህአዴግ አመራር የህዝቡን ሥልጣን ለህዝብ ለማስረከብ ዝግጁ ሆኖ ለመገኘት አልቻለም ። ይባስ ብሎ መራጩን ህዝበና የተቃዋሚ ድርጅት አባላትን በያሉበት እያሳደደ መግደል ፤ ማሰር ፤ ማሳደድና ማፈናቀልን እንደ ዋና ተግባሩ አድርጎ እየተንቀሳቀሰበት ይገኛል ። የህዝብ ፍላጎትና የኢህአደግ መሪዎች ፍላጎት የተፋፋመ ቅራኔ ውስጥ የገቡበት ሁኔታ ተከስቷል ። አገዛዙ ሥልጣኑን በምርጫው ውጤት መሠረት ህዝብ ለመረጠው ማስረከብ ሲገባው አሻፈረኝ ያለበት የኢትዮጵያ ህዝቦች ደግሞ ሕጋዊ የሥልጣን ባለቤትነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያደርጉት የሞት ሽረት ትግሉ ተፋፍሟል ። አገዛዙ ዛሬ ክምን ጊዜም በላይ በፍርሀት የተዋጠበትና ወታደራዊ ዓቅሙን እንደ ዋና ምርኩዝ አርጎ ለመጠቀም ቆርጦ የተነሳበት ክስተት ውስጥ ለመገኘት ደርሰናል ። ተወደደም ተጠላ ፤ አጠረም ረዘመም ፤ መጨረሻ ላይ ትግሉ በህዝብ ድምፅ የበላይነት እንደሚበሰር ግን ቅንጣት ታክል ጥርጥር የለንም ። "በመሆኑም ከወደቁ በኃላ መንፈራገጥ ለመላላጥ" እንደሚባለው የአምባገነኖቹ መንፈራገጥ ለመላላጥ መሆኑ ጊዜው ሳይመሸባቸው ቢገነዘቡት ይሻላቸዋል እንላለን ። በመሆኑም በማስመሰል ለመሞገስ በአገዛዙ የተዘጋጀው ምርጫ አገዛዙ የተመኘው ውጤት ባያንፀባርቅም ህዝቡ ብይኑን ሰጥቷል። በብይኑም ወደድናቸው ጠላናቸው ሰፊው ህዝብ በኢህአዴግ ላይ የቅጣት ፍርዱን አሳርፏል ። ለተቃዋሚዎችንም እምነቱን ሰጥቷል ። ምርጫ ሲባል የኢህአዴግ መሪዎች እንዳደረጉት እኔ ከተመረጥኩ ውጤቱን እቀበላሎህ ፤ ካልተመረጥኩ በጉልበት እወስደዋሎሁ የሚለው እያየነው ያለነው መንታ መንገድ ፈጽሞ ለማንም የሚያዋጣ አይደለም ።

የተካሄደው ምርጫ ያሳየው ውጤት ላንወደውም ልንወደውም እንችላለን ። ሊያስደስተንም ላያስደስተንም ይችላል። ይህ ማለት እኛ የማንወዳቸው ኃይሎች ሥልጣን ላይ መውጣትም ሊሆን እንደሚችል ምርጫው ውስጥ ከመግባታችን በፊት አውቀን መቀበል የሚገባን ጉዳይ ነው ። ዴሞክራሲ ስንል እኛ የማንፈልገውንም ጭምር ለመቀበል ራሳችን ማዘጋጀት ካልሆነ ዴሞክራሲ ትርጉም ያጣል ። የጨዋታው ሕግም ያከትምለታል ። ያኔ ሊከተል የሚችለው ጥፋት ብቻ መሆኑ ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል ። የወታደራዊ ትጥቅ የበላይነት የተወሰነ ግድያን ለመፈጸም ሊረዳ ቢችልም የሰፊውን ህዝብ ፍለጎትን በሚጻረር መልኩ ጥቅም ላይ ከዋለ ለዘለቄታው ተመልሶ ባለቤቱን እንደሚበላ ከወዲሁ መታወቅ አለበት ።

እዚህ ላይ የኢህአዴግ አምባገነን መሪዎችና እበላ ባይ ካድሬዎቻቸው ሁለት አጣቢቅኝ ውስጥ ገብተው እንደሚገኙ ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይሆንም ። ይኸውም ባንድ በኩል ምርጫውን አሸንፈናል እያሉ ሲያቅራሩ ቢሰማም በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ተቃዋሚዎች ሥልጣን ከጨበጡ የትግራይ ህዝብን ይጨርሳሉ የሚል ዘረኛ ቅስቀሳ በማራመድ ላይ መገኘታቸው ነው ። ይህ ባንድ በኩል የኢትዮጵያ ህዝብ እምነቱን አሳድሮብናል ፤ ለቀጣይ አምስት ዓመት እንድናስተዳድር መርጦናል የሚል መልእክት የሚያስተላልፍ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አይ ሥልጣን ህዝቡ ለመረጣቸው ተቃዋሚዎች ብናስረክብ እነሱ በትግራይ ህዝብ ላይ ይዘምታሉ የሚል መልእክት የሚያስተላልፍ ሆኖ ይገኛል ። የአሸንፈናል ጉራ ባዶነትን አስመልክቶ ከላይ የዘረዘርነው ስለሆነ መድገም አያስፈልገንም ። የትግራይን ህዝብ ሊጨርሱ ነው የሚለውን ግን አጠር ባለ መልክ ማየቱ ተገቢ ይሆናል ።

ተቃዋሚዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጣን ቢይዙ የትግራይ ህዝብን ለመጉዳት ይችላሉን ? በሚለው ጥያቄ ዙርያ የት.ዴ.ት መልስ ከህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎችና ካድሬዎች መልስ እጅጉን ይለያል ። ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች አገር መሆኑዋ ይታወቃል ። ኢትዮጵያን ፤ ኢትዮጵያ የሚያሰኙዋት የነዚህ ብሔር ብሔረሰቦች አጠቃላይ የጋራ እሴቶች ድምር ውጤት ነው ። ከዚህ ውጭ የሆነች ኢትዮጵያ ልትኖር አትችልም ፤ የለችምም ። በመሆኑም አንዱ ሌላውን በማስወገድ የምትፈጠር ኢትዮጵያ ልትኖር አትችልም ። ኢትዮጵያ የምትባል አገር ልትኖር የምትችለው የነዚህ ብሔር ብሐረሰቦች የጋራ ጥቅም ለማስከበር የሚችል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማቆም ሲቻል ብቻ ነው ። ዛሬ የአገሪቱን ሥልጣን ለመረከብ ህዝባዊ አመኔታ የተጣለባቸው ድርጅቶች የተሰባሰቡባቸው ፕሮግራሞችን ስንመረምር ይህንን ዓይነት ሥርዓት ለመመሥረት በሚከተሉት የፖሊሲ ንድፎች ላይ ልዩነት ቢኖራቸውም ሁሉንም ዜጋ በእኩል ተጠቃሚ የሚሆንባት ኢትዮጵያን በመገንባት መርሕ ላይ ልዩነት የላቸውም ። ይህ ማለት የአንዱ መብት የሌላውን መብት በመርገጥ ለማስከበር የሚሞክር ኃይል እንዲፈጠር የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ የዛሬቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ፈጽሞ የለም ። ከተከሰተም ነባራዊ ሁኔታው ስለማይፈቅድለት ራስን ለመግደል የተዘጋጀ ወይም አገሪቱን ለመበታትን ያቀደ ኃይል መሆን እንደሚኖርበት የሚያጠራጥር አይደለም። የዚህ ዓይነት ኃይል ይኖራል ወይም ይነሳል ብለን ባናስብም ቢከሰትስ ከሚለው ተራ መላምት ተነስተን እንኳ ብንተነትነው በራሱ ወይም ባገሪቱ ላይ ውድቀት ለማስከተል የተነሳሳ ኃይል መሆን ይኖርበታል በሚለው ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን ። ከዚህ ድምዳሜ ተነስተን ራሱን ማጥፋቱ በሚመለከት ይህ ዓይነት አመለካከት ያለው ኃይል ላገርና ለህብረተሰብ ሰላምና ብልጽግና ማነቆ ለመሆን የሚነሳሳ ኃይል በመሆኑ መመከትና መወገድ የሚኖርበት ኃይል መሆኑ የሚያወያይ አይሆንም ። ከዚህም አልፎ አገርን መበታተን እንደ አጀንዳ ይዞ የሚነሳ ኃይል ቢሆን አገርን ይዞ እንዲጠፋ የሚፈቅድለት ኢትዮጵያዊ ሊኖር ከቶ አይችልም ። ስለዚህም ይህ ኢህአዴግና የኢህአዴግ ነብሰበላ ካድሬዎች የሚያራግቡት የ"ትግሬን ለማጥፋት" አሉባልታ ተራ አሉባልታ ከመሆን የሚያልፍ አይሆንም ። የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት የሚነሳሳ ኃይል ካለ የሚያጠፋው የትግራይ ህዝብን ብቻ ሳይሆን ሁላችንም በየተራ ሊያጠፋ የሚሞክር ኃይል ስለሆን በወቅቱ መመከት ያለበት ኃይል እንደሚሆን ሁሉም ይገነዘበዋል ።

ከዚህም በተጨማሪ በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጣን እንዲረከብ የህዝብ አመኔታ የተጣለበት ኃይል እንደ ኢህአዴግ በአንድ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን ፍላጎት የሚንቀሳቀስ ኃይል ሊሆን ከቶም አይችልም ። በነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የታቀፉ ኃይሎች እንደ ኢህአዴግ በአንድ ግለሰብ ገፋ ቢል ደግሞ በአንድ ድርጅት መልካም ፈቃድ ተጠፍጥፈው የተፈለፈሉ ሳይሆን የየራሳቸውን ፕሮግራም ነድፈው እየተንቀሳቀሱ የቆዩና አገራቸውን ከውድቀት ለመታደግ በመለስተኛ ፕሮግራም አብሮ ለመሥራት በጋራ አቋም የተገናኙ መሆናቸው መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው። እነዚህ ኃይሎች በጋራ ባንድ ድምፅ የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት ለመሰለፍ የሚያስገድዳቸው ምንም ዓይነት ነባራዊ ሁኔታ የለም ። ለወደፊትም ቢሆን ከእንግዲህ ወዲህም አንድ ዘር ለብቻው የሥልጣን ባለቤት ለመሆን የሚችልበት ዕድል ያከተመለት በመሆኑ አንድ ዘር ተነስቶ ሌላውን ዘር ለመጨረስ የሚችልበት መሠረት ሊኖር አይችልም ። ለመሆኑ ተቃዋሚዎች ሥልጣን ቢይዙ የትግራይን ህዝብ ለመፍጀት የሚያነሳሳቸው ምክንያት ምንድነው ? የህወሓት ካድሬዎችም ሆኑ አለቆቻቸው ይህንን ጥያቄ አይመልሱም ። የትግራይ ህዝብ ምን ስለበደለ ነው የሚፈጀው ? እንደ ህዝብ ባገርም ሆነ በህዝብ ላይ ያደረሰው ጥፋት አለ ? መልሱ የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ ለኢትዮጵያ ክብር ልዕልናና ህልውና እንደ ሁሉም ኢትዮጵያዊ መስዋእትነት ሲከፍል የኖረ ፤ ሀገራዊና ዜግነታዊ ግዴታውን በሚገባ የተወጣና ማንንም ያልበደለ ህዝብ እንጂ የኢህአዴግ መሪዎች በሰሩት ወንጀል የሚጠየቅ ህዝብ ባለመሆኑ የሚያሰጋውም የሚያስፈራውም ምንም ጉድ

የለበትም ። በምንም ሳያሳብቡ መፍራት ያለባቸውና የሚገባቸው በአገር ክህደትና በአምባገነንነት የተዋጡት የህወሓት/ኢህአዴግና የክህደትና የአምባገነንነት መሪዎችና ልዑካን ካድሬዎቻቸውና የጥቅም ተጋሪዎቻቸው ብቻ ናቸው ። ከዚህ ውጭ ያለው የትግራይ ህዝብ ቅንጣት ታክል የሚፈራበት ምክንያት የለም ፤ ሊኖርም አይችልም ።

ታዲያ ሁኔታው እንዲህ ከሆነ የህወሓት መሪዎችና ካድሬዎች ይህንን አቋም ለማራማድ ያስገደዳቸው ምክንያት ምን ይሆን ? የህወሓት መሪዎችና ካድሬዎች በትግራይ ህዝብና ባገሩ በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ በደል መፈጸማቸውን ያውቃሉ ። ከዚህም በተጨማሪ ሥልጣን ላይ ለመቆየት አፍኖ ለመያዝና ለመቆጣጠር የቻሉት ህዝብ የትግራይ ህዝብ ነው ። በዚህ ህዝብ ላይ ያደርሱትና እያደረሱት ያለው ግፍና ፍርደ ገምድልነት ምን እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ ። በነዚህ ሁለት መሠረታዊ ምክንቶች የትግራይ ህዝብ ከነሱ ቁጥጥር ውጭ እንዳይሆን ይሰጋሉ ።

በመጀመርያ ደረጃ የትግራይ ህዝብ እነዚህ መሪዎችና ካድሬዎች ባደረሱበት ግፍና ሰቆቃ ምክንያት ዕድሉን ሲያገኝና ቀኑ ሲወጣ የመጀመርያ ተጠያቂዎች አድርጎ ሊፋረዳቸው እንደሚነሳ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ እነሱ ላይ ያለውን ቅራኔ በመለስተኛ ደረጃ እንዲይዝና ሁሉን ነገር የሚያደርጉት እሱን ለመታደግ እንደሆነ አድርጎ በመመልከት የነሱን ግፍ አሳንሶ እንዲያይና በሌላ ሓሳብ ተውጦ የነሱን ወንጀል ችላ እንዲለው ለማድረግ የሚረዳ ስለሚመስላቸው ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ የማኸል አገሩ ሁኔታ እየተባባሰ ከሄደ ለትግራይ ህዝብ እንደሚከላከሉ መስለው በመቅረብ የትግራይ ህዝብ ከጎናቸው ተሰልፎ እንደ መድኅን እንዲቀበላቸው የስነ ልቦና ዝግጅት እንዲያደርግ ለመቀስቀስም ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ ምክንያት የላቸውም ። እነዚህ የህወሓት መሪዎች የጥቅም ተጋሪ አድርባዮች እሮሮን በተመለከተ በተለያዩ የሙስና አሠራሮች በመጠቀም ያካበቱት ንዋይና ንብረት ይህ አገዛዝ ሲፈርስ አብሮ እንደሚፈርስ ስለሚገነዘቡ ለትግራይ ህዝብ የሚያስቡ በመምሰል በትግራይ ህዝብ ደም ጥቅማቸውን ለማስከበር ስለሚፈልጉ ነው ። እነዚህ ወገኖች የትግራይ ህዝብ ሰብአዊ መብት በህወሓት መሪዎችና ካድሬዎች ሲገፈፍ ይህ ሂደት ጥፋት ያስከትላል ብሎ የመናገር ድፍረት እንኳ ያልነበራቸው ሆድ አዳሪዎች ናቸው ።  ከዚህ ውጭ የትግራይን ህዝብ በወንጀለኛነት የሚያስጠይቀው የሰራው በደል የለም ። አለ የሚሉን ከሆነም እንየውና ሓሳባችንን እንስጥበት ፤ የትግራይ ህዝብም ሓሳቡን ይስጥበት ። ካልሆነ ግን የትግራይ ህዝብን ወንጀለኛ አስመስሎ በማቅረብ ሊያጠፉህ ታጥቋል እያሉ ማስፈራራትን ማቆም አለባቸው እንላለን ። የትግራይ ህዝብ ሊጠፋ ይችላል ብለን ከማሰባችን በፊት ለጥፋት የሚያስፈርጀው የሠራው ወንጀል መኖሩ መረጋገጥ አለበት ። ካልሆነ ግን ወንጀለኞቹ የህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነን መሪዎች ባገርና ህዝብ ክሕደት እንዳይጠየቁ በትግራይ ህዝብ ጀርባ ራሳቸውን ለመደበቅ የሚያናፍሱት ተራ አሉባልታ መሆኑ መታወቅ አለበት ። ባሁኑ ወቅት እነዚህ ወንጀለኛ መሪዎች በፈጸሙት ወንጀል እንዳይጠየቁ ከህዝብ ጀርባ ለመደበቅ በሚነዙት መርዛም ፕሮፓጋንዳ የሚወናበዱ የተወሰኑ የዋህ የትግራይ ተወላጆች መኖራቸው ይስተዋላል ። እነዚህ ወገኖች አላስፈላጊ ጭንቀት ውስጥ ገብተው ከህዝብ ጀርባ ራሳቸውን ለመደበቅ የሚሞክሩ ወንጀለኞች ሰለባ ከመሆን ራሳቸውን ለማዳን እንዲችሉ "ከአማራ ይጨርሳህል" ፕሮፓጋንዳ በስተጀርባ ያለውን የወንጀለኞቹን መርዝ ልብ ብለው እንዲገነዘቡ እንመክራለን ።

ይህንን ሁሉ ስንል አንድን ዘር ለማጥፋት የተደራጁና ለፖለቲካ ሥልጣን የሚወዳደሩ ኃይሎች ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሌለ ለማሳየት እንጂ ያልተገራ ምላስ ይዘው የሚለፈልፉ ባገሪቱ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ግን ወሳኝ ተራ ሊኖራቸው የማይችሉ በድርጅት የታቀፉም ያልታቀፉም ተሳዳቢዎች የሉም ለማለት አይደለም ። እነዚህ ዓይነቶቹ ተሳዳቢዎች በየትም ቦታና በየተኛውም የብሔር ተወላጆች ውስጥ እንዳሉ እንገነዘባለን ። እነዚህ ተራ ተሳዳቢዎች እየተበራከቱ ከሄዱ በሕብረተ ሰባችን ሰላማዊ ሕይወትና አኗኗር ላይ መጥፎ ጥላ ሊጥሉ እንደሚችሉም እንረዳለን ። በዚህ ምክንያትም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊያን ኃይሎች እነዚህን ልዩነትን የሚያራግቡ ግለሰቦች ሆኑ ቡድኖች ከአፍራሽ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ የማረምና የማስተማር ግዴታ እንዳለብን ከወዲሁ ልንገነዘበው ይገባል እንላለን ።

ሌላው እዚህ ላይ ባጭሩ ለማንሳት የምንፈልገው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) አባልነታችንን በሚመለከት ይሆናል ። የህወሓት መሪዎችና ካድሬዎች የት.ዴ.ት የኢዴኃኅ አባልነት እጅጉን ይቆረቁራቸዋል ። ት.ዴ.ት ከማን ጋር ህብረት መመሥረት እንዳለበትና እንደሌለበትም እነሱ ሊወስኑለት እንደማይችሉ የገባቸው አይመስልም ። ህወሓት/ኢህአዴግ ራሱን ተመልሶ መመልከት አይችልም ። ራሱን የሚያይበት መስተዋትም

የለውም ። ይህ በህወሓት/ኢህአዴግ የታየ የመጀመርያ ክስተት ሳይሆን ሁሉም አምባገነኖች የሚጋሩት ተፈጥሮ ነው ። ህወሓት/ኢህአዴግ ሲወድ ይክባል ሲያወግዝ ደግሞ እንዲያው በጭፍን ነው ። ዛሬ ትላንት ወዶ ፈቅዶ ራሱ ሕጋዊ እውቅና የሰጣቸው የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችን በህዝብ ድምጽ ስላሸነፉት ብቻ "የኢሥፓ ወንጀለኞ" እያለ ሲሰድባቸው ይሰማል ። እንዲህ ብሎ ሲሰድብ ግን ራሱ በውስጡ ስላቀፋቸው ነብሰበላ የኢሥፓ ካድሬዎችና አመራሮች የሚተነፍሰው ነገር የለም ። የአንድ ሰው የኢሥፓ ኣባል መሆን በራሱ ወንጀል ሊሆን ባይችልም ፤ እንደ ህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች አፈራረጅ ኢሥፓ መሆን ወንጀል ከሆነ ሁሉም ኢሥፓ ወንጀለኛ መሆን አለበት ማለት ነው። ወንጀል የሚሆነው የህወሓት/ኢህአዴግ አቋምን አለመቀበል ነው ከተባለ ደግሞ የራሳቸውን አቋም የሚያራምዱ ሰዎች መወንጀል ካለባቸው በሚያራምዱት አቋም እንጂ በኢሥፓነት መሆን የለበትም ማለት ነው። ዛሬ በህወሓት/ኢህአዴግ ካምፕ ውስጥ የሚታየው ውጅንብር ግን ከዚሁ የተለየ ነው ። አንድ የኢሥፓ ኣባል የነበረ የኢህአዴግን ካምፕ ከተቀላቀለ በኢሥፓነት የማይጠረጠርበት የካምፑ አባል ካልሆነ ደግሞ በኢሥፓነት የሚወነጀልበት ሁኔታ እየተገነዘብን ነው ። ይህ ዓይነት አፈረጃጀት መሠረታዊ የሕግ ሥርዓትን የሚያናጋ አደገኛ አካሄድ ነው ። አንደ ነገር ለኢህአዴግ ጥሩ ከሆነና ከኢህአዴግ አንፃር ካልታየ በስተቀር እምቢ ለኢህአዴግ አልመችም ስላለ ብቻ መጥፎ የሚሆንበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም ። ስለዚህ ኢህአዴግ ብቻ ሁለት መመዘኛ (double standard) ይዞ ለመጓዝ የሚችልበት አካሄድ በኢህአዴግ ሕግ ካልሆነ በስተቀር በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ሊኖር አይችልም ።

በዚህ መነሻ ላይ ተመርኩዘን ህወሓት/ኢህአዴግ በት.ዴ.ት ላይ የከፈተው ዘመቻ ዋጋቢስነትን ለማሳየት እንሞክራለን። የነአቶ ለገሠ ዜናዊ ካድሬዎች ት.ዴ.ት ከመኢሶን ጋር ግንባር ፈጠረ እያሉ በትግራይ ተወላጆች እንዲጠላ ለማረግ ከፍተኛ ቅስቀሳ እያደረጉ ይገኛሉ ። መኢሶንን በደርግ ጊዜ በተካሄደው ቀይሽብር ተሳታፊ ነበር ብለው ይከሳሉ ። መኢሶን ምን አደረገ ፤ ህወሓት ምን አጠፋ ፤ እገሌ ምን በደል ፈጸመ የሚሉ ጥያቄዎችን አንስተን እዚሁ በመዘርዘር ፍርድ ለመስጠት የሚያስችለን ሕጋዊ ውክልና የሌለን መሆኑ ብቻ ሳይሆን ባለንበት መድረክ ሊፈታ የሚችል ውይይትም አይደለም ። አንድ ነገር ላይ ግን በጽኑ እናምናለን ። ይኸውም ማንም ይሁን ማን ባገርና ህዝብ ላይ ለደረሰውና ለሚደርሰው ጥፋት በሕግ ፊት መጠየቅ አለበት ። ይህ ደግሞ ህወሓት/ኢህአዴግን በዋናነት ይጨምራል ። ማንኛችንም ብንሆን ላደረስነውና ለምናደርሰው ጥፋት እንደ ዜጋ ተጠያቂ መሆን ይኖርብናል ። ይህንን የሚያጣራና ወንጅሎ የሚያስፈርድ የህወሓት/ኢህአዴግ ፍርደ ገምድል ፍርድ ቤት ሊሆን ግን ፈጽሞ አይችልም ። ምክንያቱም ህወሓት/ኢህአዴግ ፍርደ ግምድልነትን እንጂ ፍትሕን አያውቅምና ነው ። ከዚህ በተረፈ ግን ፀረ-አምባገነንነትንና ክህደትን በሚደረገው ሀገራዊ ትግል ውስጥ ት.ዴ.ት አዎንታዊ አስተዋጽኦ አላቸው ብሎ ከሚያምንባቸውና መለስተኛ ፕሮግራሙን ከተቀበሉ ኢትዮጵያዊ ኃይሎች ጋር አብሮ ለመሥራት የህወሓት ፈቃድ አይጠይቅም ። እኔ ካደረግኩት ሁሉም መልካም ነው ፤ ሌሎች ካደረጉት ግን እርኩስ ነው ከሚለው የተዛባ አመለካከቱ ራሱን ቢያጸዳ ኖሮ ህወሓት ገና በጥዋቱ መኢሶን አዲስ አበባ ከደርግ ጋር ይሰራ በነበረበት ወቅት የአብረን እንስራ የልመና ደብዳቤ ጽፎ እንደነበረና የመኢሶን አመራር ተወያይቶ በግለሰብ መልስ እንዲጻፍለት ወስኖ ጥያቄህን አልተቀበልነውም የሚል መልስ እንደተሰጠው አቶ እንዳርጋቸው "ባጭር የተቀጨ ረጅም ጉዞ" በሚል መጽሓፋቸው ውስጥ አስፍረውት ይገኛል ። ከዚህም በተጨማሪ ህወሓት ፀረ-ደርግና ፀረ-ሶቭየት ሕብረት ጣልቃ ገብነት የሆነ የህብረት ግንባር እንዲፈጠር ጥሪ ባቀረበበት ውቅት ፤ የዛሬ አያርገውና ትግራይ በረሃ ድረስ ሂደው ስለ ህብረት የተወያዩት ፤ የዛሬ የኢህአዴግ እስረኛ የትላንቱ የመኢሶን አመራር አባል አቶ አበራ የማነ-አብ እንደነበሩና በወቅቱ የትግል ጥሪ በሚለው የህወሓት መጽሔት ላይ የአቋም ልዩነታቸው ተዘግቦ እንደነበረ የሚታወስ ነው ። ኣንባቢ ሁኔታውን በግልጽ እንዲያየው በTPLF 'የትግል ጥሪ' በተባለው መጽሔት በ1980 የኢትዮጵያ ኣቆጣጠር የህውሓትና የመኤሶን የጋራ መግለጫ የመጨረሻውን ገጽ እንደአባሪ ወደ መጨርሻ ኣቅርበናል። ታዲያ ነገሩ እንዲህ ከሆነ ት.ዴ.ት መኢሶን ጋር ግንባር ከፈጠረ ስሕተት የሚሆነው ፤ በፀረ ሀገራዊ አቋሙ ምክንያት ባይሳካለትም ህወሓት ከመኢሶን ጋር ግንባር ከፈጠረ ትክክል የሚሆነው በምን መለክያ ነው ? ዛሬ ዶ/ር ነገደ የኢህአዴግን "ሕገመንግሥት" እርቃኑን ስላስቀሩት የኢህአዴግ ሕገመንግሥት ከሚነካ ድርጅት ጋር የሕብረት ግንባር መፍጠር ወንጀል ነው ይሆን እየተባልን ያለነው ? ይህንን በሚመለከት ፍርዱን ለአንባቢ እንተውዋለን ። የህወሓት መሪዎችም ሆኑ ነበሰበላ ካድሬዎችን ግን ግልጽ ልናደርግላቸው የምንፈልገው ጉዳይ አለ ። ይኸም የት.ዴ.ት የትግል መስመርም ሆነ አካሄድ የመወሰን መብት ፈጽሞ እንደሌላቸሀ ማሳወቅ ነው ።

ከዚህ በተረፈ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከጫፍ እስከ ጫፍ እንደሚያውቀው በዚች ሰዓት አገራችን በአምባገነኖችና ባገር ክህደት በተበከሉ ገዥዎች ሥር እየማቀቀች ትገኛለች ። እነዚህ ገዥዎች ደግሞ የሥልጣን ወንበራቸውን ለመከላከል የሚያስችል ሆኖ እስከታያቸው ድረስ ባገርም ሆነ በህዝብ ላይ ሊፈጽሙት የማይቃጡት ወንጀል ይኖራል ብሎ መገመት የዋህነት ነው ። በህዝባዊ ንቅናቄ ከያዙት የሥልጣን ወንበር ለመውረድ የሚያስገድዳቸው ሁኔታ ሲፈጠር አገሪቱ ውስጥ እሳት ለኩሰው እርስ በርሳችን እንድንባላ አደገኛ ወጥመድ ሊያዘጋጁልን እንደሚችሉ ከወዲሁ ልንገነዘበው የሚገባ ጉዳይ መሆን ይኖርበታል ። ስለዚህም እነሱ ከሚያዘጋጁልን ወጥመድ በመውጣት አገራችንን የብሩህ ተስፋና የልማት ማእከል ለማድረግ እንድንችል ሁላችንም በአስተዋይነትና በአርቆ አሳቢነት ጎዳና እጅ ለእጅ ተያይዘን እንድንታገል ት.ዴ.ት ሀገራዊ ጥሪውን ያቀርባል ።

ድል ለህዝባዊ ትግል ! ! !
የትግራይ ህዝብ ለአምባገነኖች መሳርያ አይሆንም ! ! !
የትግራይ ህዝብ ለድሞክራስያዊ ትግል ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ወግኖ ይሰለፋል ! ! !
ሞት ላምባገነኑ ኢህአዴግና ከሃዲዎች ! ! !

ት.ዴ.ት መስከረም 1998 ዓ.ም

<u>አባሪ  በ1980ዓም የህወሐትና የመኤሶን መግለጫ የመጨረሻ ሁለት ገጾች፣</u>

